PANORAMA # XXVII

**የትዝብት አድማስ**

**ግንቦት** 30 2000 **ዓም**

***<u>ሀገርም እንደ ሰው ይሄዳል?</u>***

***<u>ሰውም እንደ ከብት በአፈላማ ይታገታል?</u>***

***የፖሊቲካ ሳይንስና የሥነ መንግሥት ጠበብት እንደሚያስተምሩት ከሆነ ÷ ሀገር ማለት÷ የታወቀ የግዛት መልከዐ-ምድር ወሰን ኖሮት÷ በውስጡ ዜጎች የሰፈሩበትና ህጋዊ መንግሥት ያለው ነው ይባላል ። በአሁኑ ወቅት÷ ኢትዮጵያ ሀገራችን ከሦስቱ መስፈርቶች ውስጥ አሟልታ ይዛለች ለማለት የሚቻለው÷ ለይስሙላም ቢሆን÷ አንዱን ብቻ ነው። ይኸውም መኖር ከተባለ÷ የሕዝቧ መኖር ብቻ ሲሆን÷ ሌሎች ሁለቱ ግን ተሟልተውላታል ማለት ያስቸግራል። ዛሬ÷ ሀገራችን ቀደም ሲል በዓለም አቀፍ ሲታወቅ የነበረው ዳር ድንበሯ የተከበረ አልሆነም። የግዛት ክልሏ ተደፍሯል ተገስሷል፤ ባለቤትና አይዞህ ባይ አጥቷል። በምዕራቡ በኩል ያለው ወሰኗ ተጥሶ ሱዳኖች ሰፊ ቃዳ መሬት ወደ ውስጥ ገብተው በመያዝ ወደ ራሳቸው ክልል አስገብተውታል። ይህም አልበቃ ብሏቸው÷ወደ ወስጥ ጠልቆና ዘልቆ በመግባት ዛፍ እየቆረጡ÷ ሳር እያጨዱ÷ ከብቶቻቸውንም ለግጦሽ እያሰማሩና በራሷ መሬት ላይ እያረሱ÷ ምርት እያፈሱ ይሄዳሉ። ከዚህም በላይ÷ የእኛን ህሞት በመፈተሻቸውም የአካባቢውን ዜጎቻችንም ሳይቀር÷ እንደ አፈ-ላም ከብት አግደው ወስደዋቸዋል። በአሁን ወቅት ከካርቱም በመኪና የስምንት ሰዓት መንገድ ርቀት በምትገኝ <u>ሲንጃ</u> በተባለች ቦታ ታስረው በስቃይ ላይ ይገኛሉ። ለከብት እንኳን በማይስማማ በረት ውስጥ ታጉራዋል። የሰው ያለህ !የሀገር ያለህ ! የጀግና ያለህ ! የአዳኝ÷ የዋስ-የጠበቃ ያለህ! እያሉ ነው። የወገን ያለህ የመንግሥት ያለህ ! ድረሱልን እያሉ በመጮኸ ላይ ይገኛሉ።***

***አባወራ የሌለው ቤት÷ አባት የሌላት ሴት ልጅ÷ ጀግና ያጣ ሀገርና ድንበር መደፈሩ መቸም ያለና የነበረ በመሆኑ÷ ምናልባት አያስገርምም ይሆናል። እኛን ግን ይህ ሁኔታ እንደ እግር እሳት ያቃጥለናል። ጥቃቱ እንደ ነዲድ እሳት ይፈጀናል። በተለይም ደግሞ÷ የቴዎድሮስን ጀግንንት÷ የዮሐንስን መሥዋዕትነት ታሪክ እየተማረ ያደገው የየካቲቱ*** 66 ***አብዮታዊ ትውልድ÷ በአሁኑ ስዓት ሀገሩ ኢትዮጵያ ያለችበትን ሁኔታ እያየ÷ የሞት ሞት ተሰምቶታል። እየተሰዋ ሀገሩን ካላዳነ በታሪክና በትውልድ ዘንድ እንደሚወቀስም ይገነዘባል። በዕርግጥም ኢትዮጵያ ሀገራችን ኢትዮጵያ የመምትሆንበት ጊዜ እሩቅ እንደማይሆን ጠላቶቿ ሊያውቁት በተገባ ነበር።***

ዛሬ ሀገራችን ያለችበትን ሁኔታ በትክክል ያልተረዳ ዜጋ ይኖራል ብለን አንገምትም፥ ለሆዱ ካደረው ፍጥር በስተቀር። በሰሜኑም በኩል ያለውንም ሁኔታ እንኳንስ ዜጎቿ ቀርተው፥ ዓለም ያወቀው በመሆኑ፥ ብዙ ገለፃ ያስፈልገዋል አንልም። በምሥራቅም በኩል ስላለው ወሰናችን ጉዳይ አስመልክቶ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መንገር፥ ለቀባሪ አረዱት ስለሚሆንብን፥ ብዙ ማለት የሚገባን ሆኖ አላገኘነውም። አሁን ያለው ሁኔታ ከቀጠል ደግሞ፥ነገ-ተነገ ወዲያ መላው ኦጋዴንን ወያኔዎቹ እንደለመዱት ከኢትዮጵያ እንደሚያስገነጥሉት ልንጠራጠር አንችልም።

በሦስተኛ ደረጃ ሀገርን ሀገር ከሚያስኘው መስፈርት አንዱ፥ በሕዝብ የተደገፈ የህጋዊ መንግሥት መኖር ነው። ይህ በኢትዮጵያ ዛሬ የለም። ኢትዮጵያንና የሕዝቧን ጥቅም የሚያስጠብቅላት መንግሥት ፈፅሞ የለም ዛሬ። ይለቁንም በስልት እያጠፉት ያለ እኩይ ብሔረተኛ ቡድን ነው ከምኒልክ ግቢ የተወሸቀው ። ብሔራዊ ሕገ መንግሥትም ይሁን፥ ህጋዊ መንግሥት የሌላት ሀገር በዓለም ውስጥ ብትኖር፥ ዛሬ ኢትዮጵያ አንዷ ነች። "የአይጥ ምስክሯ ድንቢጥ" እንዲሉ፥ የወያኔን መንግሥትነት የሚያወቅ ቢኖር፥ እንደ አሻንጉሊት የሚጠቀሙበት የበላይ ጠባቂዎቹ ብቻ መሆን አለባቸው።

በዚህም ተባለ በዚያ፥ የሀገሩን ዳር ድንበር፥ ወሰንና ጠረፍ፥ የግዛት አንድነቱን ሁኔታ፥ እንዲሁም የራሱ የሆነ ብሔራዊ መንግሥትን አስመልክቶ፥ እራሱ የጉዳዩ ባለቤት የሆነው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደፊት የሚወስነው ይሆናል። በመሆኑም፥ ዛሬ ልንለው የሚገባንና የምንችለው ፥የወቅቱን የሀገሪቱ ችግር በሁለንተናዊ መልኩ እየዘረዘርንና እየተነተንን ለሕዝባችን እያዘከርን መመዝገብና መታገል ብቻ ነው። ዛሬ፥ የሀገሩ ጉዳይ የማያንገበግበውና የማያቃጥለው ዜጋ አለመኖሩንም ስለምናውቅ፥ የአደጋውን ክብደት ለማስታወስም አንሻም። ልናደርገው የምንችለው ነገር ቢኖር፥ ዛሬም እንደትላንቱ በዓላማችን ፀንተን ትጥቃችን ሳንፈታ፥ ለብሔራዊ ነፃነትና ዴሞክራሲ ስንል ጠላትን እያነጠፉ መዋደቅ ብቻ ነው።

"የሰው ሞኝ አንድ እንጨት ያስራል" እንዲሉ፥ ለካስ ሀገርም እንደ ሰው፥ ይታመማል፥ ይከሳል፥ ይመነምናል፥ ይጨራመታል፥ ይኮማተራል፥ ቀስ በቀስም ይጠፋል ? የሀገርን ትርጉም በሚመለከት የፖለቲካ ሳይንስ መማሪያ መጻህፍት ያሰፈሩት ትርጉምና ገለፃ እንዳለ ሆኖ፥ እኛ ኢትዮጵያውያን ግን ለሀገራችን ያለን ትርጉምና አመለካከት፥ በትምህርት መስጫ ክፍል ከሚሰጠው የሀገር ትርጉምና አመለካከት በላይና የሰፋም ነው። ሀገራችንን የምናያት በሁለንተናዊ ገፅታዋ በመሆኑ፥ ትርጉማችን ሰፊና ጥልቅ ምሥጢር ያለው ነው። ኢትዮጵያ፥ ለሁሉም ዜጎቿ ፥ ተወልደው፥ አድገው፥ ኖረው፥ ሲሞቱም የሚቀበሩባት ብቻ አይደለችም። ልጆቿ፥ ሀገራቸውን የሚያይዋት፥ ከሰብዕናቸው መከበሪያ፥ ከማንነታቸው መለያ፥ ከታሪካቸው መዘከሪያ፥ ከባኅላቸው መንፀባረቂያ፥ ፥ ከዕምነታቸው መግለጫ ፥ ከነፃነታቸው ማሰከበሪያና ከጀግነነታቸው ማስመስከሪያ አኳያ ነው። ሀገራቸውን፥

ስትደኸይ የሚጠሏት፥የሚሸሿት፥ የሚከዷት ፥ ስትበለፅግ ደግሞ የሚቀርቧት እናም፥ እንደ ጥገት የሚያልቧትና የሚጠቀሙባት አድርገው አያይዋትም፡፡ የመከራዋም ይሁን የደስታዋ ተካፋዮችና ተቃዳሾች ናቸውና !

ዜጎቿ ፥ " ለእኛ ያልሆነች ኢትዮጵያ ትበጣጠስ" አይሏትም፡፡ ይህ አሳፋሪና አስተዛዛቢ አባባል፥ የነመለስና የተባባሪዎቻቸው ባኅርይና ድርጊት ሆኖ ተመመዝግቧል፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን ሀገራችንን፥ ከምጣኔ ኃብት መበልፀጊያ አንፃር፥ወይም ከምቾትና ከሀሴት ቁርኝት አያይዘን አንወስዳትም፡፡ በዘመናት የኢትዮጵያ አንድነትና የዜጎቿ ነፃነት፥ የግዛት ልዕልናዋም ይሁን ዳር ድንበሯ ታፍሮና ተከብሮ የኖረው፥ በተፈራራቂው ትውልድ ደምና አፅም ስለነበር፥ የዛሬው ተረካቢ ትውልድ፥ ለሀገሩ ኅልውናም ይሁን ለነፃነት የሚሰጠው ዋጋ ከፍተኛም የተለየም ነው፡፡

በኢትዮጵያ ሕዝብና በተፈራራቂዎች መሪዎች መካከል ያለውም ልዩነት እዚህ ላይ ይመስለናል፡፡ የኢትዮጵያ፥ ሕዝብ ሀገሩን፥ ልክ እንደ ቅርብ ጊዜ መሪዎቹ፥ በክፉ ቀን የሚከዳት፤ የሚያጋልጣት፥ ለበላዒ-ሰብ አሳልፎ የሚሰጣት ሳይሆን፥ በቁርጡ ቀን የሚጋፈጥላትና የሚሰዋላት ነው፡፡ ይህም ታሪካዊ ሀቅ፥ በ1928 ዓም እና በ1983 ዓም ተመስክሯል፡፡ ተመዝግቧል፡፡ በቅርብ ጊዜ የተፈራረቁት መሪዎቹ ግን ማንነታቸውን ያስመሰከሩት ተቃራኒው በመፈጸም ነበር ፡፡ በረዥሙ የኢትዮጵያ የመንግሥት ታሪክ ውስጥ ከላይ ለማስረጃ የተጠቀሱት ሁለት ዘመኖች/ ዓመተ ምህረቶች፥ በየወቅቱ የነበሩት መሪዎቹ የውጭ ባዕዳን ወራሪም ሆኑ፥ የውስጥ አጥፊ ጠላቶች ሲያጠቋት፥ እግሬ አውጭኝ ብለው ነው የሸሹት፡፡ ይህንን አሳፋሪ ሥራ ግን ቴዎድሮስም ይሁን ዮሐንስና ምንሊክ አለፈፀሙትም፡፡ ለብ በል አንተ ትውልድ! በኢትዮጵያ ሕዝብና በአንድ አንድ አሳፋሪ መሪዎቹ መካከል ያለው መሠረታዊ ልዩነትም አንዱ ይህ አሳፋሪ የታሪክ ሀቅ ነው፡፡ <u>የሀገርን ጥልቅ ፍቅርና ትርጉም ከኢትዮጵያ ሕዝብ የበለጠ በደሙና በአፅሙ የገለፀ፥ ያስመሰከረ ለአሳር ነው ብንል፥ ማጋነን አይሆንብንም፡፡</u>

ይህንን በታሪክ የተመሰከረ ሀቅ ከተገነዘብን ታዲያ፥ የአንድ ሀገር አልፋ-ኦሜጋው፥ ኃይሉ-ጉልበቱ፥ ሀብቱ-ንብረቱ፥ ልማት- ዕድገቱ፥ ሥልጣኔ ዕውቀቱ ፥ ሕዝቡ መሆኑ ማንም ሊጠራጠር አይችልም፡፡ ከአምባገነን ገዥዎቹ በስተቀር! የአንድ ሀገር ሕዝብ ይህንን ሁለንተናዊ ገፅታ ሊጎናፃፍ የሚችለው ግን፥ ከአምባገነኖች ጭቆና ነፃ ወጥቶ፥ በዴሞክራሲ ሥርዓት ሲተዳደር ብቻ ነው፡፡ ያለ ዴሞክራሲ ሥርዓት፥ ሁሉንም ቢያትቱት ምኞት ብቻ ሆኖ ነው የሚቀረው፡፡ ምኞት ብቻውን ደግሞ የትም አላደረሰም፡፡ ዛሬ በሀገራችን የዴሞክራሲ አለመኖርን አስመልክቶ በሰፊው የተፃፈ፥ የተነገረና ከፍተኛ መስዋዕትም የተከፈለበት በመሆኑ፥ እንደ አዲስ ክስተት ብዙ የሚባልለት ጉዳይ አይሆንም፡፡ የኢትዮጵያን ሕዝብ፥ መሪዎቹ በክፉ ቀን አጋልጠውት በመሄዳቸው ብቻ አይደለም የሚያሳዝኑትና የሚበድሉት፡፡ በሥልጣን በሚቆዩበት ወቅት ሁሉ፥ ሕዝብ ጨቆነው፥ በግፍ ጨፍጭፈው፥ ተቃዋሚዎቻቸውን ሁሉ አጥፍተው፥ ኃብት ዘርፈውና የዴሞክራሲን

ጭላንጭልን ሁሉ ደብዛውን አጥፍተው ነው የሚጠፉት:: ሕዝብን እየጨፈጨፉ ሀገረ ወዳድ ነን ቢሉ ደግሞ የማያሰቅ ቧልት ለመሆኑ ከማንም አይሰወርም:: የሚገርመው ደግሞ አዲስ መጭዎቹ፥ ሀገር አጥፎት ከሄደው አለመማራቸው ነው:: ይህ ክፉ በሽታና መጥፎ አዙሪት መች እንደሚወገድ ይገርመናል! ሀገራችን ኢትዮጵያ፥ በተፈጥሮ የታደለች፥ የተመረቀችና የበለፀገች ብትሆንም፥ በተረገሙ መሪዎቿ ደግሞ የተረገመችና የደኸየች መሆኗን ስንገነዘብ፥ የቱን ያኅል የሰው ሰራሽ ችግሮች፥ ምፀትና ሰለባ እንደሆነች ስናይ ይህ እንቆቅልሽ መቸ እንደሚፈታ ማወቅ አንችልም:: <u>በአንድ ጉዳይ ግን ዕርግጠኞ መሆንን እንፈልጋለን:: ይኸውም፥ ወያኔን ከሥልጣን አስወግዶ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መመስረት፥ የሀገራችንን የታሪክ ዕንቆቅልሽ የሚለውጠው መሆኑን ነው::</u>

<u>የወቅቱ ጥያቄ ግን መሆን የሚገባው፥ አምባገነኖችን እየወቀሱና እየረገሙ መኖሩ ብቻ ሳይሆን፥ ምን የተሻለ ሁኔታ ማምጣት ይቻላል? የሚለው ነው:: አምባገነኖችን መጣል የትግሉ ቀዳማይ አጀንዳ ወይም ዋና ተልዕኮ መሆን እንዳለበት ሁሉም የሚስማማበት ቢሆንም፥ መተኪያው ምንድን ነው? ብሎ መጠየቅ ይቅርና፥ እርስ በእርስ መስማማት እንኳን አልተቻለም በአሁኑ ወቅት!</u>

ውሉ በተሰወረበትና ቅጥ-አምባሩ በጠፋበት የትግል ሂደት ውስጥ፥ ምንም ነገር ተግባራዊ ለማድረግ አለመቻሉ ፥ የመለስን አጥፊ ቡድን ዕድሜ መቀጠልና የሀገሪቱንም ጥፋት ማጣደፍ አስችሏል::

<u>" እነርሱ ይጠፏታል እንጅ ሀገሪቱ እንደሆን አትጠፋም " የሚለው የተለምዶ አባባል፥ ለሥነ ልቦና እፎይታ ይረዳ እንደሆን እንጅ፥ ሀገሪቱማ በተጨባጭ እለት በዕለት ለጥፋት እየተዳረገች ለመሆኗ ማስረጃ የሚያስፈልግው አይደለም::</u>

እኛ ሀገር እየጠፋች ነው ስንል እኮ፥ የሕዝቡንም ዕልቂት ጭምር ማለታችን ነው:: የዜጎች መመተር፥ መጨፍጨፍ፥ መሰደድ፥ በኤድስ ቫይረስ ማለቅ፥ በረሀብ ቸነፍር መርገፍ፥ በጦርነት መማገድ፥በነፍስ ገዳዮቹ በዓጋዓዚ ወታደሮች መታጨድ ሁሉ፥ ለእኛ የሀገር መጥፋት ነው:: የብሄራዊ ሥርዓተ ትምህርት አለመኖር፥ ብሔራዊ የመማሪያ መጻሕፍት መጥፋት የሀገር ጥፋት ነው ለእኛ:: የባኅል መበረዝ፥ የታሪክ መከለስ፥ ሁሉ ሲደመር፥ የሀገሪቱ ጥፋት ነው:: የተማረው ሁሉ ሀገር እየለቀቀ ሲወጣና ባዕድን ተቀጣሪ ሀገሪቱን ሲያጥለቀልቃት ይህ የሀገር ጥፋት ካለሆነ ምን ሊባል ይቻላል? ተተኪው ወጣት ትውልድ ከውጭ በመጣ የላሸቀና ርካሽ ባኅል ተኮትኩቶ እንዲያድግ ከተደረገ፥ ነገ ሀገሪቱ ሰው አልባ መሆኗ አይደለም እንዴ? ታዲያ ይህ የሀገር መጥፋት መቅድም አይደለም?

የአየሩ ብክለት፥ የዕፅዋዕትና አዝርዕት ውድመት፥ የዛፎች መጨፍጨፍ፥ የአራዊት መጥፋት፥ የአዕዋፋት መሰደድ፥ ዘራቸው በዓለም የማይገኝ

እንስሳት መተኪያ ማጣት፥ የደኖች መቃጠል ሁሉ ሲደመር እንደ ሀገር ጥፋት ካልተወሰደ፥ታዲያ ሀገር ማለት ምኑ ላይ ነው? ዛሬ የሀገሪቱ ዋና ከተማ ብቻ ሳይሆን፥ ምድረ- ኢትዮጵያ ሁሉ ሳይቀር፥ የሰላዮች መናሃሪያ ሆኖ፥ የሀገራችን ምሥጢር እየተበረበረ፥ እየተመዘበረ፥ ውስጥ ዕቃችን ሁሉ ሳይቀር እየተዘከዘከ፥ የከርሰ-ምድር ሀብታችን ምሥጢር ሁሉ ሳይቀር ለባዕዳን መሸጥ ማለት፥ የሀገርን የነገ ኅልውና ማጥፋት አይደለም እንዴ? የሀገራችን ስትራተጂያዊ ቦታዎች የመልካ-ምድር አቀማመጦች፥ ወንዞችና ምንጮቻቸው ሳይቀሩ፥ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ወታደራዊ ዕቅድ አውጪዎች ካርታ እንዲያነሱ ሲፈቀድላቸው፥ ከዚህስ የበለጠ ሀገር ማጥፋት ምን ይገኛል?

ያለፈው ወታደራዊ መንግሥት የሀገሪቷን ብርቅዬ ዜጋና ትውልድ በሽብር ጨፍጭፎ ሀገርን ለጥፋት መዳረጉ የሚረሳ አይደለም::መለስና ግብረ-አበሮቹም ሀገራችንን በሁለንተናዊ አቅጣጫ ማጥፋታቸው ለማንም ዜጋ ግልፅ መሆኑ ባይካድም፥ የተቃዋሚው ኃይል ሀገርን ከጥፋት ለማዳንም ሆነ ለመከላከል ጠንካራ ርምጃ ባለመውሰዱ፥ ለሀገሪቱ ጥፋት የበኩሉን ተጠያቂ እንደሚሆን መረዳት አለበት:: ቢያንስ በታሪክና በመጭው ትውልድ ሳይቀር ተጠያቂ መሆኑ አይቀርም:: በታሪክና በትወልድ ሸንጎ ፊት ሁሉም በተናጠልና በጋሪዮሽ መጠየቁ አይቀሬ ነው::

<u>ሀገር ይጠፋል ስንል፥ ሀገርም እንደ ሰው ቀስ በቀስ ደክሞ፥ ተኅሳቁሎ፥ ታምሞ፥ መንምኖ፥ ከስቶ፥ ተራቁቶ፥ ተበታትኖ፥ ይከስማል ማለታችን ነው:: ይህ ደግሞ ሟርት መናገር ሳይሆን፥ በዓለም ታሪክ የታየና የተመዘገበ ሀቅ ነው::</u> አሁን ምኒልክ ግቤ መሸገው የተቀሙጡት አጥፊ ቡድኖችና የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ተባብረው በአሁኑ ይዞታቸው ከቀጠሉበትና የሚጋፈጣቸው ኃይል ካላገኙ፥ የሀገራችንም ሁኔታ ተመሳሳይ ዕድል እንዳይገጥመው ምንም ዋስትና አይኖርም::

ሀገርም እንደ ሰው ይሞታል:--ጀግና ተፈጥሮ ካላዳነው:: ጀግናን የሚፈጥረው ደግሞ ሀገርና ሕዝብ ነው:: የኢትዮጵያ ማህፀን ደግሞ ገና አልመከነም:: የሀገር ማህፀን ለምልሞ፥ ጀግና ፈጥሮ፥ ሀገር የሚድንበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም:: ሀገርም እንደ ሰው መሞት የሚችል ቢሆንም፥ ሀገርም እንደ ሰው ጀግና መፍጠሩ ደግሞ የታሪክ ሀቅ ነው:: ጀግና በጊዜና በሁኔታ ሊፈጠር ይችላል ብሎ ከመጠበቅ ይልቅ ግን፥ ጀግና ሊፈጠር የሚችልበትን ሁኔታና ወቅት እንዲመጣ ቆርጦ ሳይታክቱ መታገል አማራጭ አይኖረውም:: በተለይ ሀገርን ከጥፋት ለማዳን የሚደረገው ትግል፥ ቦታና ሁኔታን አይመርጥም:: አብሶ ደግሞ፥ ከባርነት ቀንበር ለመውጣት የቆረጠ ሕዝብ፥ ማነኛውንም መሥዋዕት ለመክፈል የሚያግደው እንደሌለ፥ የሀገራችን የረዥም ዘመን ታሪክ፥ በብዙ ምዕራፎች መዝግቦ አቀይቶናል:: ሀገርን እንደ ሰው አስገድሎ ከመቅበር ደግሞ፥ እኛ እንደ ሰው ሞተን ሀገራችንን ማዳን የበለጠ፥ የተከበረና ዘለዓለማዊ ህይወት ነው:: “ የክብር ሞት መሞት፥ ለሰማዕታት ህይወት!” የተባለውም እኮ ለዚህ ነበር! ከዚህም በቀር፥ እንዲህም ይባል ነበር እኮ ድሮ በታሪካችን !

ሀገርም ይሄዳል እግር አውጥቶ እንደሰው፥
ጀግና  ከሕዝብ ጋር ሄዶ ካልመለሰው
መሬትም ይበርራል እንደ ወፍ አሞራ፥
ትውልድ ካልመለሰው በየጦሩ ጎራ፥ እየተዋደቀ ከወገኑ ጋራ !

ኢትዮጵያ ዘለዓለማዊ ነች !!